የምፅዓቱ የምሥራች

ቅጽ 85 ቁጥር 1(985)

“ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ”
(የሐዋርያት ሥራ 1፥8)

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በአማኞች ሕይወት

(በአር. ኤ. ቶሬ/R.A. Torrey)

“ኃይል የእግዚአብሔር ነው” (መዝሙረ ዳዊት 62:11)

መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ላይ የእግዚአብሔርን ኃይል የሚሰጥ ነው። ይህ አሠራር የእግዚአብሔር የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ሰጦታ ለሰው የሚያጎናጽፍ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ሰጦታዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር ልጆች ዳግም ሲወለዱ የሚታደል ሰጦታ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ሰጦታዎችን የምንቀበለው በኢየሱስ ክርስቶስ ካለን እምነት የተነሣ በጸጋው ነው።

1. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከእግዚአብሔር የሚገኘውን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር በአማኝ ሕይወት የሚገልጽ፣ የሚያረጋግጥና የሚሠራ ነው። (1ቆሮ 12÷3)
   “ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር፦ ኢየሱስ የተረገመ ነው የሚል እንደሌለ፥ በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር፦ ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል እንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ።”
   ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገረው የታመነ ነው።
   “ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል” (ዮሐ 15÷26)።
2. መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን ያስተሰርያል። “እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ። እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል” (ዮሐ 16÷8)።
   መንፈስ ቅድስ ኢየሱስ ክርስቶስን በመግለጥ፣ ክብሩንና ጽድቁን በማሳየት፣ ፍርድንም በማሳሰብ ሰዎችን ስለ ኃጢአት ይወቅሳል።
3. መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ይለውጣል። “እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም።” (ቲቶ 3÷5)
4. መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ እርካታን ይሰጣል። “በእኔ የሚያምን፥ መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል” (ዮሐ 7÷38)
5. መንፈስ ቅዱስ ከኃጢአትና ከሞትም ያድነናል፥ ከፍርድም ይታደገናል።
   “በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና” (ሮሜ 8÷2)።
   ጌታ መንፈስ ቅዱስ ስለ ኃጢአታችን ሲወቅሰን ስምተነው ኀሰሐ እንድንገባ በኃይሉ እንድሞላን እንማጸነው።
   በተቀበልነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የክርስቶስን መልእክት ለሰው ዘር ሁሉ እናድርስ፣ ጌታም ይረዳናል።

ጌታ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስህን ሙላንና ለሰዎች ሁሉ እንትረፍ

የዚህ እትም ትኩረት ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላትና አገልግሎት ይሆናል። የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ጊዜ ያ የክብር፣ የቅድስናና የኃይል መንፈስ ከውስጣቸው እየወጣ ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር ይመልሳል፣ ከሚመጣው ዘላለማዊ ቁጣና ከዚህ ምድር ጥፋትም ያተርፋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰፋ ቃል የተናገረው አማኞች በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ወቅት የእግዚአብሔር መንፈስ በእነርሱ ውስጥ በማደር የሚሠራቸውን ተአምራቶችና አገልግሎቶች በማብራራትና በማሰረዳት ነው።

“ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም በምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።” (ሐዋርያት ሥራ 1÷8)

ይህን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጌታ በሉቃስ ወንጌል ላይ የተትረፈረፈም ብሎ ይገልጸዋል። ይህ ክቡር የእግዚአብሔር መንፈስ ለመቀበል እውነተኛ መሻትና ብርቱ ጸሎት ይፈልጋል።

ይህን መልእክትና ይህንን የመሰሉትን ሰዎች በሪች ካርማይክል (Rich Carmichle) እንዲሰሙ የሚያደርገው ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና፣ ይህንን ሰታነቡ የክብር መንፈስ የክርስቶስ መንፈስ ለክብር እንዲሞላባችሁ ፍላጎቱ ይኑራችሁ።

እንዲሞላችሁም በእውነተኛ ፍላጎት በብርቱ ጸሎት ጠይቁት፤ እርሱ ያለ ቅድመ - ሁኔታ ይሞላባችኋል። (ዮሐ 7÷37)

“ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ።” ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሰጦታ እንድንጠይቅ፣ እንድንቀበል እንድንሞላ የተሰፋ ቃል ሰለ ሰጠንና ተሰፋውን ሰለሚጠብቅ፣ መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላብን እንጠይቅ። (ሉቃ 11÷9፤ 11÷13፤ ሐዋ 2÷39)

ማንኛውንም መንፈቅ ቅዱስ የሚያሳስበንን ኃጢአት ችላ ሳንል ንሰሐ እንግባ። በዚህ ምንም መደራደርና ማቅማማት አይኖርብንም።

ያልተናዘዝነው ኃጢአት ከእግዚአብሔር ልንቀበል ያለውን ኃይልና በረከት ይይዝብናል። “በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር” (መዝ 66÷18)።

የተሰፋ ቃሉን የሰጠን ክርስቶስ የታመነ ነውና፣ መንፈስ ቅዱስን እንዲሞላብን ለሌሎችም እንድንተርፍ እንማጸነው።

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለእግዚአብሔር አገልግሎት ነው።

(በዲ. ኤል. ሙዲ (D.L. Moody)

በዮሐንስ ወንጌል በሰባተኛው ምዕራፍ የምናነበው ቃል ጌታን በምናምንበት ወቅት ሰለሚፈሰልን የሕይወት ውኃ ምንጭ ነው።

የውኃ ምንጭ ለማግኘት ሁለት መንገዶች አሉ። አንደኛው እጅግ አድካሚ የሆነ ብኩ ጊዜም የማይገኘው ጥልቅ ቁፋሮ ሲሆን፣ እጅግ የተመቸውና እንድንረካበት የሚመነጨው ደግሞ የምንጩን መገኛ ዓለት መቆፈር ነው። ለእኛም የክርስትና ሕይወት ተፈላጊውን የሕይወት ምንጭ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለማግኘት የሕይወት ምንጭ ዓለቱን ክርስቶስን መጠጋትና ከእርሱ የዓለት ምንጭ መቆፈር ነው። ይህም የሚሆነው በብርቱ በጸሎት በተሰበረ ልብ ነው።

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር መንፈስ ተምሳሌት የሆነውን የውኃ ምንጭ ለማግኘት የእግዚአብሔር ቤተሰቦች የሕይወት ምንጭ ዓለቱን ከሙሴ ጀምሮ ሲቆፍሩ፣ ሲጠይቁ፣ ሲያገኙትና ለብዙዎች መድኃኒት ሲሆን በቅዱስ ቃሉ ላይ እናነባለን። (ኢሳይያስ 44÷3፤ ማቴዎስ 5÷6)

የሕይወት ምንጭ የሆነው ክርስቶስን ተቀብለው ለሌሎችና ለራሳቸው በረከት የሆኑ ብዙዎች ናቸው።

ማንም ሰው የውኃ ጥም ባለት በረሃ ውኃን እግኝቶ የማይረካ ለተጠሙት የማያካፍል እንደሌለ ሁሉ፣ የክርስቶስን የሕይወት ምንጭ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ለሌሎች የማይተርፉ በቅዱስ መጽሐፉም ሆነ በሰው ዘር ታሪክ አልተገኙም።

ጌታችን የሚሰጠው የሕይወት ሰጦታ የተትረፈረፈ መሆኑ ያንን ሰጦታ የተቀበሉት ሁሉ ለሌሎች እንዲያጋሩት ነው (ሉቃስ 6÷38)። ይህ የጌታ ሰጦታ በሚገለጥበት ጊዜ ነገሮችን ሁሉ የሚለውጥ ታምራትና ኃይል ይገለጣል፣ ሰጦታዎቹም በአንድ ሰፍራና ለአንድ ሕዝብ ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ፣ ለሰው ዘር ሁሉ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ የሚደርሱ ይሆናሉ። (ሐዋርያት ሥራ 1÷8)

የእግዚአብሔር ሰጦታ በክርስቶስ በኩል የሚሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ሰጦታም ዋና ዓላማው የጌታ ቤት አገልግሎት እንዲሰፋ ነው።

በዚህ ክቡር ሰፍራ እንትጋ።

ሙሉና የተትረፈረፈ የጌታን ሰጦታ እንቀበል።

በእንድሪው ሙሬ (Andrew Murray)

“የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል” (ሉቃስ 7÷38፤ ዮሐንስ 6÷35)።

በአዲስ ኪዳን በሐዋርያቱ ላይ ጌታ የጀመረው እየቀጠለ ነውን? አዎን፣ የጌታችን ተሰፋ እስከ መጨረሻው የጸና መሆኑን ራሱ በሰጠው ቃል መሠረት የመንፈስ ቅዱስ ሰጦታዎችም በሐዋርያቱ ዘመን የተጀመረ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ይቀጥላል። (ማቴ 28÷20)

የውኃ ማቆሚያ ለሌሎች የሚተርፈው በየጊዜው እየተሞላ ሲቀጥል ብቻ እንደ ሆነ ሁሉ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ለሌሎች ሊያስተላልፉ የሚገባቸው አማኞችም እንዲሁ የሕይወት ምንጭ መንፈስ ቅዱስን ዘወትር ሊሞሉ ይገባቸዋል።

በነቢዩ ዕንባቆም ዘመን የታዩት ዓይነት ፍሬዎች በእግዚአብሔር በረት ሞላ ወይም መስማሪያ ባይገኙም፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ በጌታ ታምኖ የእግዚአብሔርን የሕይወት ምንጭ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ሁል ጊዜ የተዘጋጀና በጌታ የታመነ መሆን ይገባዋል። (ዕንባቆም 3÷1)

በዘመናት ሁሉ ጌታ በእርሱ የታመኑትንና የሚጠባበቁትን ከተሰፋውና ከሚሰጣቸው የሕይወት ውኃ ምንጭ አጉድሎ አያውቅም። (ኢሳይያስ 40÷3፤ 1ጴጥ 2÷1)

እግዚአብሔር እርሱ በሰጦታዎች ሁሉ የተሞላና ሁሉ በሁሉ የሆነ ጌታና አምላክ ሰለ ሆነ፣ እርሱን ታምነን በረከቱን ወይም የተትረፈረፉ ሰጦታዎቹን እንጠብቅ። (2ቆሮ 1÷2፤ ቆላ 1÷1)

የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል በረከቶች እንዳይገድሉብን ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮችን እናስብና እንፈጽም። እንዳልገባቸው ያለ ጌታ ምንም ነገር ማድረግ እንደማንችል ተረድተን፣ እንጠይቀው። የጌታ ሥራ የሚፈጸመው በእምነት ሰለ ሆነ፣ እምነት እንዲጨመርልን እንጠይቅ። (መዝ 121÷15፤ 1ዮሐ 5÷1-)

የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የእግዚአብሔር መጎናጸፊያ ነው።

በሮበርት ሞንየር (Robert Boyd Monyer)

“ከኤልያስም የወደቀውን መጎናጸፊያ ወሰዶ ውኃውን መታና፦ የኤልያስ አምላክ እግዚአብሔር ወዴት ነው? አለ፤ ውኃውንም በመታ ጊዜ ወዲህና ወዲያ ተከፈለ፤ ኤልሳዕም ተሻገረ” (2ኛ መጽሐፈ ነገሥት 2÷14)

በሰው አስተሳሰብ ኤልሳዕ የጠየቀው ጉዳይ በጣም አስቸጋሪና ሊሆን የማይችል ነበር። ሆኖም ግን፣ ይህንን ጥያቄ የኤልያስን መንፈስ አጥብቆ በመሻት ጌታን ሰለ ጠየቀ፣ እግዚአብሔር መለሰለት። የኤልያስ መጎናጸፊያ የእግዚአብሔር ክብር የነበረውን ሁለት እጥፍ ተቀበለ።

ኤልሳዕ ወጣቱ ነቢይ ታላቁ ኤልያስ ወደ እግዚአብሔር ከማረጉ በፊት በብርቱ ጥያቄና ፈተና ተሞልቶ ነበር። ያቀረበውም ጥያቄ እጅግ ከባድና አስቸጋሪ ነበር። ሆኖም ግን፣ ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም ተብሎ እንደተጻፈው፣ ኤልሳዕ ከነቢዩ ኤልያስ እግዚአብሔር ያጎናጸፈውን የክብርና የአገልግሎት መጎናጸፊያ በመቀበል፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ትልቅ ኃይልና በረከትን ተቀበለ። ብዙ ኃይልና የእግዚአብሔር ታምራት የሚገለጡት የእግዚአብሔር ሰዎች በከፍተኛ ቁዘማ፣ ብሶትና መሪር ሁኔታ ውስጥ ሲገቡ ከሚያቀርቡት የጸሎት መቃተት የተነሣ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ይህ ጉዳይ ተመሳሳይ ነው። የክብር ጌታ፣ ሁሉን ቻይ ኢየሱስ ክርስቶስ በጠላቶቹ ተላልፎ ተሰጥቶ ከተገደለ በኋላ ብዙ ተሰፋ ያደረጉበት ሐዋርያቱና ደቀ መዛሙርቱ እጅግ ተሰፋ ቆርጠው በጽኑ ሐዘን፣ በእምባና በጸሎት ተሰብሰበው በኢየሩሳሌም በሚጸልዩበት ወቅት እጅግ ያልታሰበ የሰውን ልብ የነካ ‘’. . . ሰዎች ምን እናድርግ?’’ የሚል ጥያቄ ያስከተለ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወረደ (ሐዋርያት ሥራ 2÷41)።

እስከ ዛሬ ድረስም የጌታ ቃል አልተለወጠምና፣ በሚደርሰብን መከራ፣ መሰደድና መገፋት ላይ በጋራ ጌታን በብርቱ ጸሎት እንጠይቀው። በዚህ ለሀገራችንና ለዓለም የሚተርፍ የጌታን መጎናጸፊያ እንቀበላለን።

የመንፈስ ቅዱስ የክብር አገልግሎት

በጆን ዌስሊ (John Wesley)

“ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ፥ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም?” (2 ቆሮ 3÷7)።

የክብሩን ወንጌል አገልግሎት የሚያካሂዱ አማኞችና አገልጋዮች ሊጸለይላቸው ይገባል። በተለይ፣ በዚህ የወንጌል አማኞችን ልዩ ልዩ ፈተናዎች እጅግ በሚገዳደሩበት ወቅት ሁላችንም ትክክለኛው የወንጌል ቃል በትክክለኛዎቹ አስተማሪዎች ይዘጋጅና ለትምህርት ይቀርብ ዘንድ መጸለይና መደገፍ፣ ትክክለኛውን ወንጌል ከፍቅረ ንዋይና ተመሳሳይ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍልስፍናዎችን በክርስትና ሰም ከሚያስተምሩ መጠበቅ ይገባናል።

በዚህ ወቅት የቀደመው የወንጌል አማኞች በሳልና ርቱዕ ትምህርት እንዲመለስ፣ ከቅዱስ ቃሉ የሚጣረሰው ማንኛውም ቡድንና አገልጋይ እንዲነቁና እንዲስተካከሉ ማወጅ እጅግ አስፈላጊ ነው (ሰቆቃው ኤርምያስ 5÷21፤ መዝ ዳዊት 63÷2፤ ትንቢተ ኢሳይያስ 51÷9) ።

ሰዎች ከሰይጣን ወጥመድ ይወጡ ዘንድ ዛሬ ማገልገል ያለብን እጅግ እየከበደ የመጣው በትክክለኛው የወንጌል ትምህርት የተመራ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት በመጓደሉና ከአሳሳች ሰሑት ትምህርት ጋር የወንጌል አማኞች መሪዎችና ምእመናን በመጣመራቸው ነው።

የመንፈስ ቅዱስ የክብር አገልግሎት ለማካሄድ በወንጌሉ የጋራ አገልግሎት ያላቸውን ሁሉ በሚቻለው ለማሳተፍ ተገቢ ጥረት ማካሄድ ያስፈልጋል። እንዳችን ለሌላው ወንጌል አማኝ የአንድ አካል ብልቶች መሆናችንን በመረዳት፣ በእያንዳንዱ የአገልግሎተ ወቅት የጋራ ኃላፊነት መፈጸም ያስፈልጋል። የወንጌል አገልግሎት ለእግዚአብሔር ክብር በትክክለኛው መልኩ ሲካሄድ የእግዚአብሔር መንፈስ የሰዎችን ልብ እየነካ “ምን እናድርግ?” ብለው በመጠየቅ የክርስቶስን ማኅበር

የሚቀላቀሉበት ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል። (ሐዋርያት ሥራ 2÷37)

የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎትን ክብር የሚያጎድፈው ኃጢአትና ኃጢአት ብቻ በመሆኑ፣ በየዕለቱ የኃጢአት ኑዛዜ ሕይወት ኖሮን የክብሩን አገልግሎት

መንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑ

በቴዎድሮስ ኢፕ (By Theodore H.Ep)

መንፈስ ቅዱስ በማንም ሰው ላይ፣ በማያምኑት ላይ ጭምር፣ አሳዛኝ ያልተገባ ንግግርና አስተያየቶች መሰጠትና ማሳዘን አይደገፍም።

<u>መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝኑ ጉዳዮች</u>

“ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ” (ኤፌሶን 4÷30)።

መንፈስ ቅዱስን ማሳዘንም ሆነ ሌላውን ኃጢአት በመናገር ወይም ባለመናገር በእንቅስቃሴዎቻችንም ኃጢአት መፈጸም እንችላለን።

“መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ” (ኤፌሶን 4÷31)። መዋሸትና እውነትን አለመናገር በእንደበት ብቻ ቢመሰለንም፣ በአስተያየታችንና በአደራረጋችን ይህን ክፉ እንሠራለን።

ከአፋችን የሚወጣው ቃል ሁሉ ክርስቶስን የሚያስከብር፣ የሚሰማንን ሁሉ የሚባርክና የሚያድን መሆን ይገባዋል (ኤፌሶን 4÷29)።

በእንደበት እግዚአብሔርንና ፍጥረቱን መበደል እጅግ ቀላል ሲሆን ፣ እንዴ ከተናከሩ በኃላ ማስተካከሉ እጅግ ይከብዳል።

እግዚአብሔር በቅዱስ ጥምቀት አዲስ ፍጥረት ሲያደርገን መልካም ሥራ እንድንሰራ አንደበታችን እርሱን ፈጣሪያችንን እንዲያከብር ፍጥረቱ ሁሉ ልንባርከና ልናመሰግንበት (ያዕቆብ መልእክት 1÷26፣ 3÷6)

የእግዚአብሔር ልጆች ጌታን የሚያስከብር፣ ሰዎችን ሁሉ የሚባርክ ንግግር በመተው፣ በመርገም፣ በመሳደብና በከንቱ ንግግር ከተሞላን፣ መንፈስ ቅዱስን እናሳዝናለን (ኢሳይያስ 11÷2፤ ዮሐ 14÷17)።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ የተቀበልኩት ራስን የመግዛት የጥበብ የእውቀት መንፈስ እንጂ፣ የሰድብና የከንቱ ንግግር ነውር አይደለም (2 ቆሮንቶስ 4÷13፤ ሮሜ 8÷)

የእግዚአብሔር መንፈስ የፍቅር መንፈስ ሲሆን፣ ላመኑት የሚያድለው ፍቅርን፣ ጭምትነትንና ጨዋነትን ነውና፣ በእርሱ በቅዱስ መንፈሱ በየዕለቱ በመሞላት በእግዚአብሔር ፍርሃት መንፈስ ቅዱስን ሳናሳዝን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እንመስክር (1 ጢሞ 1÷7፤ ዕብራውያን 10÷29)።

መንፈስ ቅዱስን አታጥፉ

(በጆርጅ ሶልታው/George Soltau)

“መንፈስን አታጥፉ” (1 ተሰሎንቄ 5÷19)። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ቃል የሚያሳስበን የፍቅርና የመዳን፣ የጨዋነትና የክብር መንፈስን እንዳናጥፋ፣ በማይገባ የኃጢአት ሰፍራና ግንኙነት ውስጥ በመሆን እንዳናረክሰው ነው።

የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስን የምናጥፋባቸው ብዙ ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣረሱ ልምምዶች ሲኖሩ፣ ዋናዎቹ ግን፦

1. ቸልተኝነትና እኔነት
2. ኃጢአትን በድፍረት መለማመድ

3. የመንፈስ ቅዱስ እሳት እንዳይቀጣጠል ክፉ ሐሳብና ሥራ መቸለስ ናቸው።

በእነዚህ ክፉ የሰንፍናና የኃጢአት ድርጊቶችና ንግግሮች ሰንሰማራ ራሱ የታተምንበት መንፈስ ቅዱስ ለሕሊናችን የሚነግረን ሲሆን፣ ቅዱስ ቃሉና የሚመለከቱንና የሚያዳምጡን ወገኖች ያስጠነቅቁናል። እነዚህን ማስጠንቀቂያዎች እምቢ በማለት በኃጢአታችን ከቀጠልን ግን ከሕይወት ወጥተን ለእግዚአብሔር ቁጣ እንዳረጋለን።

“ጌታ ሆይ፣ እሳቱን ላክልን” በጄነራል ዊልያም ቡት፣ የሳልቬሽን አርሚ አገልግሎት መሥራች የመንፈስ ቅዱስ ጥሪ (BY General William Booth, Founder of Salvation Army)

የኤልያስ አምላክ ጩኸቴን ስማ! እሳቱን ላከልኝ በሕይወት እንድንቀጥል ወይም እንዳንጠፋ እሳቱ ይለቀቅልን!

ኃጢአት ሁሉ እንዲቃጠል፣ የእግዚአብሔር ክብርና ብርሃን እንዲመጣ፣ የመንፈስ ቅዱስ እሳት ይምጣ።

የሰጠኸን ተስፋ ይፈጸምልን። ዳግመኛ ጴንጤቆስጤ (ጸራቅሊጦስ) ታምር በምድራችን ይሰፈንልን። ደካማ ልባችን እንዲበረታ ከሰይጣንና ከዓለም የሚያድነን ቅዱስ እሳትና (አዎን፣ ለኢትዮጵያውያን እንቆቅልሽ መፍትሔ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ እሳት) ይምጣልን-- አሜን።

የእግዚአብሔር ታማኝነት በኖርዌይ ሚሲዮናዊ ሜሪ ምንሰ

በ1922 ዓ.ም ጌታ የተጠቀመባት የኖርዌይ ሚሲዮናዊ ሜሬ ሞንሰን በሰሜን ቻይና የትልቅ መንፈሳዊ መነቃቃት መሣሪያ ነበረች።

ሜሬ ጌታ እንደሚጠቀምባት ሙሉ እምነት የነበራት ሴት ስትሆን፣ ሄስትጋራ የመርከብ ጠላፊዎች እገታ ሳይበግራት ጌታ ያዘጋጀላትን የወንጌል አገልግሎት በሚገባ ፈጽማለች።

ለሜሪ ጌታ የሰጣት አገልግሎት የተሰፋ ቃል (ሚልክያስ 3÷18) ነበር። “ተመልሳችሁም በጻድቁና በኃጢአተኛው መካከል፣ ለእግዚአብሔር በሚገዛውና በማይገዛው መካከል ትለያላችሁ።”

ሜሪ በመርከብ በምትጓዝበት ወቅት ገንዘብ ከያዙት ውስጥ ብቸኛዋ ነበረች። ይህን ያወቁ ዘራፊዎች ሜሬን ለማገት ቢበቁም፣ እግዚአብሔር ባደረገው ጥበቃ ከክፉ አጋቾች ተርፋ በሰሜን ቻይና አንዱና ትልቅ የነበረው የመንፈሳዊ መነቃቃት እንዲካሄድ የጌታ መሣሪያ ለመሆን በቅታ ነበር።

ጌታ በዚህ አስደናቂ ጥበቃው ሜሪን ከክፉ ጠላቶች ታድጎ ለሥራው ስለ ተጠቀመባት፣ ሜሪ ጌታን በቅዱስ ቃሉ ባርካለች። “በተከበበ ከተማ የሚያሰደንቅ ምሕረቱን በእኔ የገለጠ እግዚአብሔር ይመስገን” (መዝሙረ ዳዊት 30÷21)።

እግዚአበሔር ሜሬን ከክፉ ጠላቶች እንደ ታደጋት የተመለከቱ የመርከቡ ተሳፋሪዎች፣ ካፒቴኑና ባልደረቦቹ መሬት ላይ ተንበርክከውና ጌታን ከልብ አመሰግነው ነበር።

ዛሬም በዘመናችን በልዩ ልዩ የዓለማችን ክፍሎች፣ በተለይም ወንጌን መሰበክ በሕይወት ላይ ጉዳት ሞት በሚያስከትልባቸው ሰፍራዎች፣ የጌታን ቃል በድፍረት ስለሚመሰክሩት የወንጌል መልእክተኞች (ሚሲዮናውያን) ጌታን እናመሰግናለን። ከነቤተሰቦቻቸው ጌታ በጥበቃው እንዲጋርዳቸው እንጸልይላቸዋለን። “እግዚአብሔር ግን እንዲህ ይላል። በኃያላን የተማረኩ ይወሰዳሉ፥ የጨካኞችም ብዝበዛ ያመልጣል” (ኢሳይያስ 49÷25)።

እግዚአብሔር ዛሬም እንደ ትናንቱ መንፈሳዊ መነቃቃትን ያመጣል።

(ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ፣ የአማርኛ አስተባባሪ)

“ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለም ያው ነው” (ወደ ዕብራውያን 13÷8)

የዓለም ሁሉ መድኃኒታችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሳይወለድ በፊት እምቅድመ ዓለም ለዘላለም የነበረው ዛሬም ሕያው ጌታ ሆኖ በቅዱስ መንፈሱ የእግዚአብሔርን ሥራ በአማኞች ሁሉ ላይ ይሠራል። በብሉይ ኪዳን ዘመን ከግብፅ ባርነት የእስራኤልን ሕዝብ ነጻ ሲያወጣ በበረሃ በውኃ ጥማት እንዳያልቁ ውኃን ከዓለት ያፈለሰ፣ ከፈርዖን ሰራዊት እየታደገ ለተሰፋ ምድር ያበቃቸው፣ የአዲስ ኪዳን አዲሱ እስራኤል የሚባለውን ከሁሉም ነገድና ዘር፣ ከአይሁድ ጭምር፣ በእርሱ ያመኑትን ክርስቶስ ዛሬም ይምራል፣ ከክፉ ይጠብቃል። በተሰበረ ልብ በንስሐ ወደ እርሱ በሚመጡት ላይ መንፈስ ቅድስን እያፈሰሰ መንፈሳዊ መነቃቃትን ያከናውናል።

በመጨረሻው ዘመን በሴትና በወንድ ባሪያዎቼ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ለዚህ ለዘመናችንም ይሠራል፣ ይፈጸማል። (ትንቢተ ኢዩኤል 2÷2)

የክርስትና መልካም ጅማሬ በጌታ ትእዛዝ በኢየሩሳሌም የተጀመረው እንደ ተሰፋ ቃሉ እስከ አለም ዳርቻ እየተሰፋፋ ብዙዎችን በወንጌል በመድረስ ላይ ሳለ፣ የሰይጣን ልጆች በማሰመሰል ገብተው የክርስቶስን ማኅበር አስነውረዋል። ክርስትናን የግፍ፣ የባርነትና የቅኝ አገዛዝ ክፉ ሥራዎች መሣሪያ አድርጓል። ሆኖም ግን፣ ይህን ክፉ ድርጊት እንደሚፈጽም በሐዋርያው ቃል አስቀድሞ የተነገረውን (ሐዋርያዊ መልእክት አያሌ መንፈሳዊ መነቃቃቶችና ተሐድሶዎች በምድራችን ተካሂደዋል። ዛሬም ብዙ አሳቾች በክርስትና ሰም ግፍን፣ ዘረኝነትንና ፍቅረንዋይን ቢፈጽሙም፣ የጌታ እጅ ከማዳን አላጠረችም። በእውነተኛው ወንጌል እንትጋ፤ መንፈሳዊ መነቃቃት እናካሂድ።

ዓለም አቀፍ የጸሎት ርእሶችና ምስክርነቶች

በታንዛንያ በቅርቡ ከተደረገው ምርጫ በኋላ ሥልጣን የያዘው መሪ ተቃዋሚዎችን፣ ወንጌል አማኞችን ጭምር፣ በማሰር ላይ ይገኛል።

ሆኖም ግን፣ ትራንስ ወርልድ የተባለው የወንጌል ሬዲዮ አገልግሎት በታንዛንያ ለሚገኙት ነዋሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ወንጌል በማሰራጨት ላይ ይገኛል። ለዚህ መልካም ጅማሬ ጌታን እያመሰገንን፣ ለሬዲዮ አገልግሎቱ ጸሎታችን ይቀጥል።

<u>በአርጀንቲና ስለ ተካሄደው የወንጌል ሥራ</u>

<u>ጌታን እናመሰግን</u>

በአርጀንቲና ዋና ከተማ ቦነስ አይረስ በተደረገ ትልቅ ኮንፍራንስ/ክሩሴድ 75 ሺህ ሕዝብ ወንጌል የሰማ ሲሆን፣ 9ሺህ ሰዎች ጌታ ክርስቶስን አምነዋል።

ላመኑት አርጀንቲናውያን እንጸለይ፤ ወንጌሉን ለሌሎች እንዲመሰክሩ ጌታን በማመስገን በጸሎት እንደግፋቸው።

<u>በሄይቲ በሥቃይ ላሉ ሕፃናት እንጸለይ</u>

በሄይቲ ወደ ጎዳና የሚወጡት ምስኪን ሕፃናት ቁጥር እየጨመረ ይገኛል። ከትምህርት እየተሰተጓጎሉ በጎዳና ተዳዳሪነት ያሉትን የሄይቲም ሆነ የራሳችንን የኢትዮጵያን ሕፃናት ጌታ እንዲታደግ፣ እንዲጠብቅና እንዲባርክ እንጸልይ።

የደኅንነት ምሰክሮች

1. ኃጢአተኛ መሆናችንን ያመንን ሰዎች ይህን የእግዚአብሔር ቃል ያለበትን ጽሑፍ በነካን ጊዜ በንስሐ ወደ ጌታ እንቅረብ (ሮሜ 3÷23፣ 6÷23)።
2. የእግዚአብሔርን ይቅርታና ምሕረት በጸሎት እንጠይቀው (ትንቢተ ኢሳይያስ 55÷7)።
3. ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ መሆኑን በቅዱስ ቃሉ እንደተጻፈው አምነን ለመከተል የክርስትና ጉዞን እንጀምር (ዮሐንስ ወንጌል 1÷12)።
4. ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነቱን አምነን ከተቀበልን በኋላ፣ በቅርባችን ወደሚገኙ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ሰም ወደሚያጠምቁና ወደሚያሰተምሩ ማኅበራት እንቀላቀል። (ማቴ 28÷19፤ ሐዋርያት ሥራ 2÷)

የምጽአቱ የምሰራች ማስታወቂያዎችና ምስክርነት

ከናይጀሪያ

በየጊዜው ለምትልኩልኝ የምጽአቱ የምሰራች መንፈሳዊ ጋዜጣ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ጋዜጣው የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል እየገለጸ ስለሚያሰረዳኝ እጅግ ተባርኬበታለሁ።

ከአውስትራሊያ

በመንፈሳዊ ሕይወቴ ለሚያሳድገኝ በየጊዜው ስለምትልኩልኝ የምጽአቱ የምሰራች እጅግ አመሰግናለሁ። በዚህ አገልግሎት ሕይወቴ ተባርኳል።

ከኢትዮጵያ

በየጊዜው ለምትልኩልኝ የምጽአቱ የምሰራች ጋዜጣ በጣም አመሰግናለሁ። በቅርቡ የላካችሁልኝን የእንግሊካን እትሞች ከሴሚነሪው አጠገብ ባለው የመጻሕፍት መደብር ደርሶኛል። ሌሎችም ወዳጆቼ ስለሚጠቀሙበት፣ ሳታቋርጡ በመላክ ተባበሩኝ።

ከእንግሊዝ

የምጽአቱ የምሰራች በዚህ ከተማችን ካሉ ወገኖች ጋር በብዙ እየጠቀመን ይገኛል። እግዚአብሔር አምላክ አብዝቶ ይባርካችሁ።

ለየምጽአቱ የምሰራች እንባቢዎች

የምጽአቱ የምሰራቹን በመተርጎም ለሕዝባችን መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲረዳ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በነጻ በማሰራጨት ላይ እንገኛለን።

በየጊዜው ለምትልኩልን ምስጋናና ማበረታቻ ለሁላችሁም መመለስ ስለማንችል፣ በዚሁ ምስጋናችን ይድረሳችሁ።

የአገልግሎቱ ብቸኛ ገቢ የእንባቢያን ስጦታና መዋጮ በመሆኑ የእቅማችሁን በፖስታ ቤት ሀዋላ በመላክ ተባበሩን።

የምጽአቱ የምሰራች አገልግሎት

የአማርኛው አስተባባሪ፡- ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ

በኢትዮጵያ ተጠሪ፡- ብርሃኑ ጥርሣማ

አርታኢ፡- ዘነበ ገብረሐና

ታይፕና ዲዛይን፡- እቤኔዘር የጽሕፈት ሥራ፣ መካኒሳ

በሶላር ማሚያ ቤት ታተመ።

በነጻ የሚሰጥ፣ ስልክ 0993154034

Amharic Herald of His Coming

የፖ.ሣ.ቁጥር. /P.O.Box 8986

አዲስ አበባ፣ Addis Ababa, Ethiopia.